## "ሚስቴ UNHCR ቢሮ በር ላይ በፖሊስ ድብደባ የ5 ወር ነፍሰ ጡር አስወረደች"




**ባለቤቷ ኡስማን አብዳ**



ኢትዮጵያዊያን በየመን UNHCR ቢሮ እና የቢሮውን ደህንነት ይጠብቃሉ በተባሉ ፖሊሶች የሚድረስባቸው ግፍ ዕለት ከዕለት እየጨመረ ነው

ከዚህ በፊት"በየመን UNHCR ያስገነጥላል ኤምባሲ ያጨበጭባል" በሚለው ጽሁፌ ላይ እንደገለጽኩት ለደረሰብን በደል መፍትሄ ይሰጠን ብለው UNHCR በር ላይ የተቀመጡ ባልና ሚስቶች በፖሊስ ድብደባ የ5 ወር እርጉዝ አስወርዳለች:: እሷ በጥሩ ጤንነት ላይ ባለመሆኗ ከባለቤቷ ኡስማን አብዳ ጋር ቃለ-ምልልስ አድርገናል: : እንዲህም ያለ ግፍ አለ ወይ? ያሰኛልና እነሆ አንብቡት..... ስለዚሁ አሰቃቂ ግፍ እውነተኛነትም በስተመጨረሻ የተያያዘውን የክህምና ማስረጃ ይመልከቱ።

ጥያቄ:- ኢትዮጵያ እያለህ ዝዋይ ታስረህ እንደነበር ነግረኸኛል ለምንድን ነው የታሰርከው?

ኡስማን:- የኦነግ ደጋፊ ናችሁ በማለት ዝዋይ ደሴት ላይ ከመታሰሬ በፊት አማሬሳ ለአንድ ዓመት ብዙዎች ታስረናል:: አማሬሳ በታሰርን ሰዓት በአንድ አመት ከ70 ሰው በላይ ሞቶብናል:: ዝዋይ ተሻጋግረን 3 አመት ከታሰርን በኋላ ፍ/ቤት አቆሙን::

ጥያቄ:- በሶስት አመት ውስጥ የነበረው ሁኔታ እንዴት ነው? ቀይ መስቀልስ አልጎበኛችሁም?

ኡስማን:- ቀይ መስቀል መጥቶ ጠይቆናል:: መዝግቦናል:: የነበረውን ስቃይ ዛሬ ባወራው ለማመን ይከብድሀል::

ጥያቄ:- በኋላስ እንዴት ወጣችሁ?

ኡስማን:- በ1993 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተነስቶ ... የተማሪዎች አመጽ በመላ ሀገሪቱ ሲቀጣጠል እኛ ተለቀቅን:: ቦታው ለተማሪዎቹና ለሌሎቹ አመጹን ያቀጣጠሉ ወጣቶች መቅጫ ስላስፈለገ ተፈታን:: ያኔ ቀይ መስቀል ሲጎበኙን መዝግበውን ስለነበረ ወደ አዲስ አበባ ሄድን:: በምዝገባው መሰረት ወረቀት ጻፉልን:: ወደ ቤተሰብም ከገባን በኋላ መቀመጥ አልቻልንም:: በትልቁም በትንሹም ይተናኮሉን ጀመር:: የተሰጠን ስም በአካባቢው ጥሩ እይታ ስላልፈጠረ አላኖረንም:: ህዝቡም ተጠራጠረን:: ሀገር ለቅቄ ወደ ሱማሊያ ገባሁ::

ጥያቄ:- የስደት መነሻ ምክንያትህ እንዳለ ሆኖ ሱማሊያ ውስጥስ ምን ነበር የገጠማችሁ? የነበረውን ጫናስ እንዴት ተቋቋማችሁት?

ኡስማን:- ከኢትዮጵያ መንግስት ተልከው እዛ የሚቀመጡ ሰላዮች አሉ:: እነሱን

ፍርሀትም ጥንቃቄም አርገን አንችላቸውም:: ሱማሊያ መኖር አልቻልንም:: ያለን አማራጭ ወደ የመን መሻገር ነውና በባህር ተሻገርን::

ጥያቄ:- ለኢትዮጵያዊያን ሱማሊያ መኖር አስቸጋሪ ነው:: ኑሮው ይከብዳል:: ከሀገርህ ያልተሻለ ሀገር ላይ መኖር ነጻነት ፍለጋ እንደሆነ እኔም አንተም እናውቀዋለን:: አንተስ ኑሮውን እንዴት ገፋኸው?

ኡስማን:- ሱማሊያ በጣም..በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ነው::ሬሳ በየመንገዱ ተጋድሞ ነበር:: የእኛን ሴቶቸ እየደፈሩ... መናገሩ ያሳፍራል:: ከሴቶች አልፈው ወንድ ሁሉ እየደፈሩ ታያለህ:: ለሁለት ለሶስት ሆነው ይደፍራሉ:: ተርበን..ተደብድበን በግፍ ተጭነን ነው የባህር ጉዞ የጀመርነው:: ጀልባዋ ላይ የሚሰሩት 3 ሱማሌዎች ጠጥተው ሰክረው በዱላ ጭንቅላት..ጭንቅላታችንን እያሉ ያስኛቸውን ወደ ባህር እየወረወሩ ተስቃይተን ነው የየመንን መሬት የረገጥነው::

ጥያቄ:- በስንት አመተ ምህረት ነው ወደ የመን የገባኸው?

ኡስማን:- በአውሮፓ 2003 ዓ.ም

ጥያቄ:- የየመንን መሬት ከረገጥክ በኋላ በቀጥታ ወደ UN ነው ያምራኸው?
ኡስማን:- ለአንድ አመት አልቀረስ የተባለው ካምፕ ውስጥ ቆየሁ::

ጥያቄ:- በ UN ወይስ በቀይ መስቀል በኩል ካምፕ ገባህ?

ኡስማን:- ቀይ መስቀል የሰጠኝን ወረቀት አሳይቼ ቆይ መፍትሄ ይስጥሀል እየተባልኩ ምንም መፍትሄ ሳይሰጠኝ አንድ አመት ተቀመጥኩ:: ከዛ ጠፍቼ ወደ ሰነዓ መጣሁ:: አንድ ወር እንደሞላኝ ከምተኛበት በረንዳ ላይ ያዙኝና ጅዋዛት/ኢሚግሬሽን እስር ቤት/ ወሰዱኝ: :

ጥያቄ:- ይሄ ማለት በ 2005 እኔና አንተ እስር ቤት በተገናኘን ሰዓት ነው?

ኡስማን:- አዎ! .. ያኔ አንተ ጣራው በብረት ስኩዌር ሆኖ ተሰርቶ ለጸሀይ መሞቂያ ተብሎ በተሰራው ውስጥ ነበርክ .. እኔ ግን የነበርኩበት ቦታ በጣም ችግር ነው:: ለቀይ መስቀል ብንጮህ ትንሽ አገዙን እንጂ ዩ.ኤን. ዝም ነው ያሉን:: ከእስር እንደወጣሁ UNHCR ስሄድ እምቢ አሉን:: ቀይ መስቀል ሁለት ጊዜ ደብዳቤ ጽፈው ስጡን:: በዚህ ምክንያት ተቀበሉን::

ጥያቄ:- ምንድን አደረክ ብለው አሰሩህ?

ኡስማን:- ለኦነግ ከዚህ ሰው እያሰባሰብክ ወደ ኤርትራ ትልካለህ ነበር የተባለኩት::

ጥያቄ:- እርግጠኛ ባልሆንም እስር ቤት ከተገናኘን በኋላ ነው አግብተህ የወለድከው:: ከዛ በኋላ የልጆችህ እናት ኢፍቱ ታስራ ወደ ሱማሊያ የተወሰደችበት ሁኔታ ነበር:: እንዴት ወደ ሱማሊያ ወሰዷት?

ኡስማን:- አማርኛ ከእኔ የባስ አትችልም:: [ከእሱ ጋርም በአስተርጓሚ ነው ቃለ-ምልልስ ያደረግነው] ሱማሌ ነሽ አሉና ወደዛ አሳፈሯት::

ጥያቄ:- አንተ ጋብቻችሁን ህጋዊ አድርገህ ፎርም ላይ ሞልተህ መታወቂያ /mandate/ አልተሰጣትም ነበር? እንዴት ተጠረዘች?እሷ ስትታሰር አንተ የት ነበርክ?

ኡስማን:- እሷ ሳትሄድ/ሳትጠረዝ/በፊት እኔ ሶስቴ ታስሬ ነበር:: ሶስት ጊዜም በብር አስፈታችኝ:: ስራም አጣሁ በአጋጣሚ ከእሷ ጋርም በትንሽ ነገር ተጋጨን:: ተለያየንና ሌላ ቦታ መኖር ጀመርኩ:: በዚህ ወቅት ነው ለአንቺ ስራ አገኘንልሽ እናስገባሽ አሏት:: እስከ 9 ሰዓት በሞቶ ዶላር እስራለሁ አለቻቸው:: ከዛ በተሻለ እናስገባሽ ብለው አስቸገሯት:: ስራ ስትሆን ልጆቹን የምታስቀምጥበት ጠባቂዎች ጋር ልታመጣ ስትሄድ እዛ ጠበቋት:: ስራ እናስገባሽ ብለው ካናገሯት ውስጥ አንዱ እና ፖሊሶች ሁለት ናቸው:: ከነልጆቿ መኪና ላይ አስወጧት:: እስር ቤት ወሰዷት:: ከዛ ተጫወቱባት::

ጥያቄ:- ተጫወቱባት ስትል ግልጽ አይደለም?

ኡስማን:- ደፈሯት.. አንገላቷት... ደሟን እያዘራች ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷት:: ከተወሰን ቀን በኋላ መታሰሯን ሰማሁ:: የት እንዳለች ሳፈላልግ አንቺ ኢትዮጵያዊ አይደለሽም ሱማሌ ነሽ ብለው ወደ በርበራ ወደብ አሳፍረዋታል ተባልኩ:: የማደርገው ጠፉኝ:: እሷ ግን ከበርበራ ወደብ ወደ ሃርጌሳ UNHCR ቢሮ ሄዳ የገጠማትን ብትናገር እኛን አየመለከተንም ይሄ መታወቂያ እዚህ አይሰራም:: የመን ሄደሽ አመልክቺ አሏት:: ያላት አማራጭ ከሁለት ልጆቿ ጋር ወደ ቦሳሶ መሄድ ስለሆነ ሄደች::

ጥያቄ:- አንተ እዚህ ምን አይነት እርምጃ ወሰድክ? ማለት ምን እንቅስቃሴ አደረክ? UN አመለከትክ?

ኡስማን:- ብዙ ነው የሞከርኩት:: አንድ እዚህ ሀገር የኦሮሞዎች ተወካይ ነኝ የሚል ሰው ሱልጣን የሚባል አለ:: "ሚስትህ ከሱማሊያ ወደ ኢትዮጵያ እንድትገባ የኤምባሲ ወረቀት እንልካለን አታስብ አንተም ከፈለክ ወደ ኢትዮጵያ እንመልስሃለን አሁን ወደ ሱማሊያ ደውለን እሷን እንዲያስገቧት እናድርግ"አለኝ:: አልተስማማሁም:: በሌላ በኩል ዩ. ኤን እና ቀይ መስቀል አመልክቻለሁ:: ወረቀትም አስገብቻለሁ::

ጥያቄ:- ወደ ሱማሊያ ሲልኳት ሁለት ልጆቿም አብረው ነበሩ? የስንት አመት ልጆች ነበሩ? ቦሳሶስ የነበረ ቆይታዋ ምን ይመስላል?

ኡስማን:- አዎ! ... አብረዋት ነው ወደ ሱማሊያ የተወሰዱት:: የመጀመሪያው ልጄ 2 አመት ከ6 ወር ሁለተኛው 1 አመት ከ5 ወር ነው:: ከሀርጌሳ ወደ ቦሳሶ እንደገባች ታማ ወደቀች:: ሲያነሷት መታወቂያዋን ሲያዩ አጋጣሚ አንድ የሚያውቃት ሰው አገኛት:: እሱም ለእኔ ወደ የመን ደወለልኝ:: በዚህን ጊዜ ነው ሱማሊያ ውስጥ ያለችበትን ሁኔታ በትክክል ያወኩት:: ወዲያው ቀይ መስቀል ገብቼ ሱማሊያ ቦሳሶ መሆኗን አሳወኩኝ:: እነሱም ቦሳሶ ወዳለው ቀይ መስቀል ተደዋወሉ:: ዩ.ኤን ግን አያገባንም አሉኝ::

ጥያቄ:- ከሱማሊያ ህክምናዋን ጨርሳ ወደ የመን እንዴት ተሻገረች?

ኡስማን:- እዛ ያለው ቀይ መስቀል በረዳት ብር ጤንነቷ መለስ ሲል ወደ የመን ለመሻገር ጀልባ ላይ ከሁለት ልጆቿ ጋር ወጣች:: ላንድ ሳምንት ባህር ላይ ቆየች::

ጥያቄ:- ከሶማሊያ የመን ያለው የባህር ጉዞ ቢበዛ .. ቢበዛ 41 ሰዓታት እንደሚፈጅ ነው የማውቀው እንዴት ሆኖ ነው አንድ ሳምንት የፈጀባት? በእግር ነው እንዴ የመጣችው?

ኡስማን:- አይ! .. ማዕበል ተነስቶ አቅጣችጫቸውን አስቀየራቸው:: አቅጣጫ ሰለሳቱ ማዕበሉ ከቆመ በኋላ ጉዞ ሲጀመሩ ያሉበትን አውቀው መንገዳቸውን እስኪያስተካክሉ

ብዙ ሰው አለቀ:: ከ 54 ሰው በላይ ሞቷል:: የእግዚአብሄር ነገር ከነልጆቿ ተረፈች:: ቀይ መስቀል ነግሬ ስለነበር እነሱ ባህሩ ድረስ ሄደው ተቀበሏት:: እሷ ራሷን ስታ ወድቃ ልጆቹ ተኝተው አገኙዋቸው::

ጥያቄ:- በልጆቹ ላይ የደረሰ ነገር የለም?

ኡስማን:- እስከ አሁን በጤንነታቸው የደረሰ ችግር የለም::

ጥያቄ:- ኦ... ኦ... ቀይ ማስቀል ብዙ ተባብሮሀል ማለት ነው? በቀጣይስ ምን አደረጉላቸው?

ኡስማን:- ቀጥታ ወደ ሳኡዲ ጀርመኒ ሆስፒታል ወስደው ለ 1 አመት ነጻ ህክምና ባጀት አወጡና አሳከሚት:: የሚያሳዝነው ግን UNHCR ትብብር ሊያደርግላት አልቻለም:: አልፈለገም:: ይህ ስብዓዊነት የጎደልው መድሎ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ላይ የሚፈጸም በመሆኑ ታውቀዋለህ? ሁሉም ያውቀዋል:: ከባህር ከወጣች ጀምሮ ለ4 ወር ያህል በተከታታይ ወረቀት ብናስገባ ምንም መፍትሄ ሊሰጡን አልቻሉም:: ከዚህ በላይ ምን ችግር አለ? መፍትሄ ስጡኝ ብላ እዛው UNHCR መግቢያ በር ላይ ተቀመጠች:: መፍትሄ ካልተሰጠኝ አልነሳም ብላ በቆርቆሮ በካርቶን መጠለያ ሰርታ 3 ወራት ብትቀመጥም ዞር ብለው ሊያዩዋት አልፈለጉም::

ጥያቄ:- ሚስትህ UNHCR በር ላይ ስትቀመጥ ክሁለት ልጆችዋ ጋር ነበር አንተ ለምን አብረሃት አልተቀመጥክም?

ኡስማን:- እዛ አካባቢ ካገኙኝ ፖሊሶች እየደበደቡኝ ተቸገርኩኝ:: እሷ ሴት ስለሆነች አይመቷትም ብለን ነበር:: ከ3 ወር በኋላ ግን ከUNHCR በር ላይ እንድትነሳ ያርጉዋት በዱላ ደብድበው ነው?

ጥያቄ:- ማነው የደበደባት?
ኡስማን:- የUNHCR ቢሮ ሰራተኞች ፖሊስ ጠርተው አስነሱልን አሏቸው:: መፍትሄ ካልተሰጠን አልነሳም ስትል ቆምው እያዩ ፖሊሶቹ ደበደቡዋት:: ደም በደም ሆነች:: የ5 ወር እርጉዝ ነበረች አስወረዳት:: ተደብድባ እንኳን ህክምና እምቢ ብለው ቀይ መስቀል ነው ያሳከማት ወረቀቷን ማየት ትችላለህ::

ጥያቄ:- በዚህ ጉዳይ ላይ ሁማን ራይት መግለጫ አወጠቶ ቢሮውንም አናግሮ ነበር ምን ምላሽ ሰጡህ?

ኡስማን:- እኛ የአንተ ነገር አቅቶናል:: አሁንም ለUNHCR ቢሮ ፋክስ እናደርጋለን አሉኝ:: ጠየቁም እስካሁን መልስ አልተሰጣቸውም::

ጥያቄ:- አሁን የሚስትህ ጤንነት በምን ሁኔታ ላይ ነው?

ኡስማን:- ህክምና እየተከታተለች ነው:: ደም አልፎ .. አልፎ ይፈሳታል:: ውጋት ያዘኝ ብላ አብሶ አየሩ ቀዝቀዝ ሲል ትጮሀለች:: ያው እነሱ የፈቀዱትን ህክምና ነው የምታደርገው በግል አቅም የለንም:: የጤና ችግር ይዟት እስከ አሁን ከአልጋ አልተላቀቀችም:: ከ6 ወር በላይ ተኘታለች:: ለልጆቼ ብቻዬን ስርቼ ለማሳደግ ባለመቻሌ ችግር ላይ ነኝ::

ቸር ይግጠመን
የአምላክ ስራ ግሩም

SAUDI GERMAN HOSPITALS GROUP
JEDDAH - ABHA - RIYADH - MADINA - SANA'A
WE CARE

مجموعــة مستشفيــات السعــودي الألمانــي
جدة - أبها - الرياض - المدينة المنورة - صنعاء
نحن بعون الله نرعاكم

DATE : ____________________

# تقـريـر طبـي
# MEDICAL REPORT



التاريخ : ____________________

PIN: SY01.0000115389

Final Diagnosis:

5 months pregnancy with dead fetus.

Hospital Course:

The patient pass smoothly without complication.

Diagnostic & Therapeutic Procedure performed including operation done:

5 months pregnancy with dead fetus, induction of labour was done and the patient delivered dead fetus.

Results of positive investigations:

DR Profile.

Condition at the time of discharge & Follow up Instructions:

The patient was discharge on March 28, 2009 in good general condition.
Come back to OPD after one week.

Discharge Medications:

`Augmentin 1g tab oral every 12 hours for 7 days.
`Pregnacare tab oral every 12 hours for 3 days.
`Pregnacare tab oral every 24 hours for 30 days.

Dr. Samira Al Twaity
OB/Gyne Consultant
//OG15

Dr. Abdullah Hussien
Chief Medical Operations

Dr. Samira Hezam Al Towaity
Cons. OB/Gyn
OG 15

SAUDI GERMAN HOSPITAL
We Care
Medical Record

28/3

//: Mo

ص.ب. : ٨٧٩٤ هاتف : ٣١٣٣٣٣ ١ ٠٠٩٦٧ فاكس : ٣٣٣٩٠٠ ١ ٩٦٧ -صنعاء الجمهورية اليمنية
P.O.Box : 8794 - Sana'a Tel :+967 1 313333 - Fax :+967 1 333900 E-mail: sghsanaa@y.net.ye

SAUDI GERMAN HOSPITALS GROUP
JEDDAH - ABHA - RIYADH - MADINA - SANA'A
WE CARE

مجموعــة مستشفيــات السعــودي الألمانــي
جدة - أبها - الرياض - المدينة المنورة - صنعاء
نحن بعون الله نرعاكم

28-Mar-2010 10:58

# تقــريــر طبــي
# MEDICAL REPORT

DATE : ____________________ التاريخ : ____________________

**NAME** : MOHAMED,IFTU ABDOSH
**PIN** : SY01.0000115389
**Nationality** : ETHOPIA
**Age/Sex** : 25 Year(s) Female
**Room/Ward** : DR7 (DELIVERY ROOM)
**Date of Admission** : 25-Mar-2010 15:08
**Date of Discharge** : 26-Mar-2010 15:18
**Company** : INTERNATIONAL COMMITEE OF RED CROSS

Diagnosis :5 months pregnant with dead fetus.

---

Chief complaint:

G3+P2+0, 5 months pregnancy with dead fetus.

Reason for admission:

For delivery.

Significant diagnosis and co-morbidities: (Initial diagnosis)

5 months pregnancy with dead fetus.

Significant physical and other findings: (History of present illness)

The patient was admitted to our hospital for dead fetus delivery. She is pregnant 5 months with history og vaginal bleeding before 2 days with loss of fetal movement on exaination. There is vaginal bleeding. Cervix open 1cm. By U/S baby is dead, no amniotic fluid, retroplacental haemoatoma.

Significant Medications & Other management lines:

Dextrose 5%. 500cc IV.
Augmentin 1.2gm IV every 12 hours.
Tramadol vial 5 tab.